8ኛ ዓመት ቁጥር 14
8th Year No. 14

ባህር ዳር ሰኔ 30/1995 ዓ/ም
Bahir Dar, 7th July , 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 4.93
Unit price ----------

ማውጫ	Contents
አዋጅ ቁጥር 88/1995 ዓ/ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ	Proclamation No. 88/2003 The Amhara National Regional State Mass Media Agency Establishment (Amendment) Proclamation No. 88/2003.

አዋጅ ቁጥር 88/1995 ዓ/ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሀገሙመንግሥቱ በተደነገገው መሠረት በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ባሉት የክልላችን የብዙሃን መገናኛዎች የተለያዩ ሃሳቦችና አመለካከቶች በህብረተሰቡ ውስጥ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ብዙሃን መገናኛዎቹ ይበልጥ የተጠናከረ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲሁም የህግ ጥበቃ እዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፣

የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን አስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ/ም መሠረት ተጠሪነቱ ለክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 56/1993 ዓ/ም የተቋቋመውን የብዙሃን መገናኛ ድርጅት አቋም መርምሮ ማሻሻልና የተጠሪነት ለውጥ እንዲኖረው አድርጉ በአዲስ መልክ ማደራጀት በማስፈለጉ፣

Proclamation No. 88/2003
A proclamation to provide for the Amendment of the Amhara National Regional State Mass Media Agency Establishment Proclamation.

WHEREAS, it is necessary to provide a more consolidated institutional and operational autonomous as well as legal protection to the government owned mass media of our Region with a view to ensuring free expression of different opinions and views among the public in accordance with the provision of the Constitution;

WHEREAS, it is necessary to reorganize the Mass Media Agency having examined and improved its stand as well as to make a change of its accountability, which was established being accountable to the Information Bureau of the Region by proclamation No. 56/2000 pursuant to the provision of the Reorganizing of the National Regional state Executive organs and Determination of their powers and Duties proclamation No. 60/2001;

ክልላዊ የመንግሥት ብዙሃን መገናኛዎች በክልላችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖራቸውን የላቀ ሚና እና አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአገልግሎት አድማሳቸውን ለማስፋት የሚያስችላቸውን ተቋማዊ ጥንካሬ እንዲያገኙ ማድረግ በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it is necessary to give institutional strength that enables the Regional State Mass Media to broaden out the scope of their services by considering the major roles and contributions they have on the economic, political and social activities of our Region;

ዓለማዊና አገራዊ ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ፍላጐት እያደገ መምጣቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት የህብረተሰቡን የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች በቅርበትና በስፋት በመዘገብ ሊጫወት የሚችለውን ሚና በመረዳት ድርጅቱ አሁን ካለበት በተሻለ መልኩ ተዋቅሮና በአገሪቱ ካሉ ሌሎች የብዙሃን መገናኛዎች ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ ማድረግ በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it is deemed necessary to reorganize the Agency in a better way so as to make it discharge its responsibilities efficiently being competitive with other Mass Media in the Country with due consideration that the global and national fastest information exchange demand is increasingly growing as well as with cognizance of the role that the Regional Mass Media Agency can play a role in reporting the day-to-day activities of the society closely and in-depth;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል፣

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it, under Article 49 sub-Article 3/1 , hereby proclaims as follows:

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

PART ONE

GENERAL

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 88/1995 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This proclamation may be cited as " The Amhara National Regional State Mass Media Agency Establishment (Amendment) proclamation No. 88/2003."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

2. Definitions

Unless the context requires otherwise in this proclamation:

1. «የብዙሃን መገናኛ» ማለት በሬዲዮና ቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጦችና በመጽሄቶች አማካኝነት መረጃ/ኢንፎርሜሽን/ የማሰባሰብ፣ የማዘጋጀትና የማሠራጨት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ የዜና እና የኮሮግራም ሥራዎችንና መጣጥፎችን በማጠናቀር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለህዝብ የሚያሠራጩ ወይም እነዚህኑ በቀጥታ ለሚያስተላልፉ ሌሎች ተቋማት የሚያከፋፍሉ ተቋማት ናቸው።

1. "Mass Media" mean institutions which collect, produce and disseminate information through radio, television as well as news papers and magazines; gather and disseminate to the public works of news and programs as well as articles in various means or distribute same to other institutions which transmit them directly;

2. "ጋዜጠኛ" ማለት በብዙሃን መገናኛ ድርጅት ውስጥ በአዘጋጅነት፣በአርታኢነት፣ በዘጋቢነት፣ በካርቱን አዘጋጅነት፣ በግራፊክስ ባለሙያነት፣ በፎቶግራፍ አንሺነት፣ በተንቀሳቃሽ ፊልም አንሺነት፣ በፊልም ኤዲተርነት፣ በፊልም ዳይሬክተርነት፣ በቴክኒሻንነት ወይም ዜና እና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በማሠራጨት ሙያ የተሠማራ ማናቸውም ሰው ነው።

3. "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሠጠው አካል ነው።

4. " ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የብዙሃን መገናኛ የሥራ አመራር ቦርድ ነው።

3. ስለመቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብዙሃን መገናኛ ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ/ ህጋዊ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ መንግሥታዊ ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ይሆናል።

4. የድርጅቱ ዋና መ/ቤት

1. የድርጅቱ ዋና መ/ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።

2. ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ ቅርንጫፎችና ወኪል ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

5 ዓላማዎች

ድርጅቱ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፦

2. "Journalist" means any person who is engaged as producer, editor, reporter, cartoonist, graphic artist, photographer, cameraman, film editor, film director, technician or who is involved in gathering, organizing and disseminating news and information in the Mass Media Agency

3. " Person" means any natural or juridical person.

4. " Board" means the Management Board of the Mass Media established pursuant to this proclamation.

3. Establishment

1. The Amhara National Regional State Mass Media Agency (hereinafter referred to as "The Agency") is hereby reestablished as autonomous governmental Agency having juridical personality.

2. The Agency, being established for unspecified period of time, shall be accountable to the council of the Amhara National Region.

4. Head Office of the Agencey

1. Head office of the Agency shall be in Bahir Dar.

2. The Agency shall have branch and agent offices within and outside the Region as may be necessary.

5. Objectives

The Agency shall have the following objectives:

1. በፌዴራሉና በክልሉ ህገ-ጉ መንግሥታት እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ሐሣብን በነፃ የመግለጽ ነፃነትን ማበረታታት፣

2. የክልሉ ህዝብ ለመረጃ ቅርበት እንዲኖረው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን እንዲያገኝ ማድረግ፣ በዚህም በዋና ዋና የአገሪቱና የክልሉ ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባትን መፍጠር እንዲችል መስራት፣

3. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አጋዥ ሚና መጫወትና በህብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት ማበረታታት።

ክፍል ሁለት

ስለ ድርጅቱ አወቃቀርና ሥልጣን

6. ድርጅታዊ አቋም

1. ድርጅቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የሥራ አመራር ቦርድ፣
   ለ. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣
   ሐ. ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣
   መ. ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች።

2. ድርጅቱ ሥራውን ለማከናወን በሥሩ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የሕትመት /ፕሬስ/ እና የዜና አገልግሎት የብዙሃን መገናኛ ዘርፎች ይኖሩታል።

7. የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለክልሉ ህዝብ ጠቀሜታ ያላቸውን አስፈላጊ ዜናና ዜና ነክ መረጃዎችና በኘሬስ ውጤቶች፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ማሠራጫዎች ለህዝብ ያስተላልፋል፣ ለዚህም እንዲረዳው እንደ አስፈላጊነቱ መደበኛ የጋዜጣ፣ የመጽሄትና ሌሎች ህትመቶች እንዲሁም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ኘሮግራሞች እንዲኖሩት ያደርጋል፣

1. Encourage free expression of ideas in accordance with the Federal and Regional Constitutions as well as with other relevant policies, laws, regulations and directives;

2. Create conducive conditions to enable peoples of the Region to have access to up date and accurate information, and thereby exercise to bring about national consensus on main affairs of the Country and the Region.

3. Play a supportive role in the economic, political and social activities of the Region and foster the development of democratic culture within the society;

PART TWO
STRUCTURE AND POWER OF THE AGENCY

6. Structure of the Agency

1. The Agency shall have the following bodies:

   A. Management Board
   B. General Manager
   C. Deputy Manager
   D. Other necessary Departments

2. The Agency shall have branches of Mass Media under it so as to carryout radio, television, press and news services.

7. Powers and Duties of the Agency

The Agency, pursuant to this proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Disseminate to the public news and related materials which have importance for the peoples of the Region through press products, radio and television transmissions and to the enhancement of same it causes to have regular news paper, magazine and other publications as well as radio and television programs as deemed necessary;

2. የመንግሥትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች፣ ፖሊሲዎችና ህጐች ለህዝብ ያስተዋውቃል፤ ህዝቡም በስትራቴጂዎቹ፣ በፖሊሲዎቹና በህጐቹ ላይ ሐሳቡን እንዲሰዋወጥባቸው፣ እንዲመክርባቸውና አስተያየቱን እንዲሰጥባቸው በዚህም ብሔራዊ መግባባት ላይ እንዲደርስ ምቹ የሚዲያ መድረኮችን ይፈጥራል፤

3. የክልሉ ነዋሪ ህዝብ ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤ ለማጐልበት የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ከተሞክሮዎች ጋር እያዛመደ ያቀርባል፤

4. ነፃ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፤ የሚመለከታቸውንም አካላት በመጠየቅ ያጣራል፤ ውጤቱንም መልሶ ለህዝብ ይገልፃል፤

5. የህዝቡን ጠቅላላ እውቀት የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጐቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ጽሁፎችንና የሬዲዮም ሆነ የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን እየሠራ በተለያዩ ዘዴዎች ያሠራጫል፤

6. ወቅታዊነት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ተከታትሎ ይዘግባል፤

7. የፎቶግራፍና የተንቀሳቃሽ ምስል ዶክመንቴሽን፣ የህትመትና የማስተዋወቂያ /Advertising/ አገልግሎቶችን ይሠጣል፤

8. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የህትመት አገልግሎቶችን፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ማቀናበሪያና ማሰራጫዎችን፣ የዜናና መረጃ ማስተላለፊያ ወይም ማሸጋገሪያዎችን እንዲሁም ለተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውሉ ሌሎች ተቋማትን እና መሣሪያዎችን በተገቢው ሥፍራ ይተክላል፣ ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤

9. ለሚሠጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤ እንደአስፈላጊነቱም በከፊልም ሆነ በሙሉ ከክፍያ ነፃ አገልግሎት ሊሠጥ ይችላል፤

10. በአገሪቱ ህግ መሠረት በአገር ውስጥና በውጪ አገር ካሉ ተመሣሣይ ድርጅቶች ጋር ዜናዎችንና መረጃዎችን ለመለዋወጥም ሆነ የሥልጠና እና የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ የሚያስችሉትን የሥራ ግንኙነቶች ይመሠርታል፤

2. Publicize government strategic directions, policies laws as well as create favorable Media forum for the public to exchange views, discuss and comment on the strategies, policies and laws and thereby to attain National consensus;

3. Present variety of programs by correlating with experiences, which foster human and democratic rights awareness of inhabitants of the Region.

4. Entertain free public opinions and suggestions as well as investigate of same by interviewing concerned bodies and announce the result back to the public thereof;

5. Produce and disseminate a variety of articles and radio as well as television programs which would develop the general awareness of the public and meet its entertainment needs through various methods;

6. Follow up and report on the current economic, political and social affairs;

7. Deliver photography and film documentation, publication and advertisement services;

8. Install, establish and organize in appropriate locations essentials for operating publication services, radio and television programs production and transmission, news and information transmitter or relay as well as other institutions and equipment applicable for similar services and administer same thereof;

9. Collect equitable service charge and exempt partially or in full when deemed necessary;

10. Establish work relations, pursuant to the Country's laws, with similar domestic and foreign agencies in order to make it possible to exchange items of news and information as well as to undertake training and experience sharing;

11. በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙና የድርጅቱን ቴክኒካዊ አቅም ለማጎልበት ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ካላቸው ድርጅቶች ጋር በክልሉና በአገሪቱ ፖሊሲዎችና ህጐች መሠረት አብሮ ይሰራል፤

12. የክልሉ የብዙሐን መገናኛዎች ስለሚስፋፉበትና በተስማሚ ቴክኖሎጂ ስለሚደራጁበት፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ስለሚሰጥበት ሁኔታ በማጥናት ሐሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሳል፤

14. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሀጋውያን ተግባራትን ያከናውናል።

ክፍል ሶስት

ስለ ድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ እና ስለሥራ አስኪያጆች

8. ስለቦርዱ አወቃቀርና ተጠሪነት

1. ድርጅቱ ከሰባት የማያንሱና ከዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ባሉት የሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።

2. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላትና የህብረተሰብ ክፍሎች ተውጣጥተው በክልሉ ር/መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ም/ቤት ይሠየማሉ።

3. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል።

4. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ም/ቤት ይሆናል።

5. ቦርዱ ስብሰባውን በሚያካሂድበት ወቅት ድምጽ የሌለው ቃለ-ጉባኤ ያዥ ለሥራው ቅርበት ካለው የሥራ ክፍል ሊያስመድብ ይችላል።

9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

11. Work together, according to policies and laws of the Region and the country, with organizations found at home and abroad as well as with those which are voluntary to contribute assistance to develop the technical capacity of the Agency;

12. Undertake studies and forward recommendations as to how the Regional Mass Media expanded and equipped with suitable technologies in order to deliver prompt and efficient services; implement same up on approval thereof;

13. Own property, enter into contract, sue and be sued;

14. Perform other legal functions necessary to achieve its objectives.

PART THREE

BOARD OF MANAGEMENT AND MANAGERS OF THE AGENCY

8. Structure and Accountability of the Board

1. The Agency shall be directed by a managing board having members not less than seven and greater not nine.

2. The chairperson and members of the Board shall be appointed by the Council of the Region upon their presentation by the Head of Government selected from the appropriate governmental organs and sections of the society.

3. The Manager of the Agency shall be the member and secretary of the Board.

4. The accountability of the Board shall be to the Council of the Region

5. The Board may cause the assigning of a minute's person with no vote from a related work division whenever it holds its sessions.

9. Powers and Duties of the Board

The Board, pursuant to this proclamation, shall have the following powers and duties;

1. ድርጅቱ የብዙሃን መገናኛዎችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ህጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ማድረጉን ያረጋግጣል፤

2. በህዝብ ሊታወቁ የሚገባቸው የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በድርጅቱ ልዩ ልዩ የብዙሃን መገናኛዎች አማካኝነት በወቅቱ መተላለፋቸውን ይከታተላል፤

3. ድርጅቱ በሚሠጣቸው አገልግሎቶች የክልሉ ህዝብ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ ይገመግማል፤ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንባቸውን መንገዶች ም በየጊዜው እየፈተሸ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለድርጅቱ መመሪያዎችንና አቅጣጫዎችን ይሠጣል፤

4. ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በተመለከተ ከህዝብ በሚነሱ ስሞታዎች እና በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተገቢ ማብራሪያዎ ችን እንዲሠጥ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ስሞታዎችንና ቅሬታዎችን መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ ይሠጣል፤

5. ድርጅቱ በብሄር ብሄረሰቦች፣ በጾታ፣ በሃይማኖት እና በፖለቲካ አመለካከቶች መካከል ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ወገኖች ሚዛናዊ የመረጃ ሽፋን መስጠቱን ይቆጣጠራል፤

6. በክልሉ የብዙሃን መገናኛ ተቋማት የሚሠራጩ ትን የዜና፣ የሐተታ፣ የኘሮግራም፣ የመጣጥፎች እና ሌሎች ዘገባዎችን አጠቃላይ ይዘት ይገመግማል፤ ስለሚሻሻሉበትም መንገድ መመሪያ ይሰጣል፤

7. የድርጅቱን ጋዜጠኞች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የቅጥር፣ የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅሞች ይወስናል፤ የአፈፃፀምና የሰራተኛ አስተዳደር ማኑዋልም ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ መርምሮ ያፀድቃል፤ ስራ ላይ እንዲውልም ያዛል፤

8. የድርጅቱ የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ማኑዋል ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ያፀድቃል፤ ሥራ ላይ እንዲውልም ያዛል፤

1. Ensure that the Agency implement polices, laws, regulations and directives in the Region, which are pertinent to the Mass Media;

2. Monitor the prompt transmission of government polices, laws, regulations and directives, which have to have acquaintance with the public through various mass media of the Agency;

3. Evaluate that to what extent peoples of the Region to have benefited from services rendered by the Agency as well as give directions and guidelines to the Agency for implementation by frequently examining ways which promote better utilization;

4. Call on the Agency to give relevant explanations on complaints raised and grievances lodged by the public concerning duties that the Agency discharges pursuant to this proclamation and examine the complaints and grievances and thereby make its own decisions as deemed necessary,

5. Supervise that the Agency provides balanced Media coverage to all compatriots without discrimination on the basis of nation, nationalities, sex, religion and political outlooks;

6. Evaluate the over all content of news, analysis, programs, articles and others reports which are disseminated by the Mass Media Institutions of the Region and give guideline for the betterment of same thereof;

7. Decide on the recruitment, salary scale and fringe benefits of journalists, technical professionals and supporting staff of the Agency; approve upon examination Performance and Administration Manual by causing to have prepared and submitted to it and thereby order the implementation of same.

8. Approve, having caused prepared and submitted to it, the Finance and Property Administration Directive of the Agency; order for the implementation of same thereof;

9. የድርጅቱን መዋቅር ገምግሞ ያፀድቃል፣ ሥራ ላይ እንዲውልም መመሪያ ይሠጣል፣

10. የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እንደዚሁም ዓመታዊ፣ የካፒታልና መደበኛ በጀት አቅድና ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

11. ድርጅቱ ከመንግስትና ከውስጥ ገቢ የተመደበ ለትን በጀት ባግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

12. ድርጅቱ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሳል፣

13. በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት የድርጅቱን ም/ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ የድርጅቱን ሌሎች ከፍተኛ አመራር አካላት አመላመልና ምደባ ይወስናል፣

14. ድርጅቱን በሚመለከቱ በሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፣

15. የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ዘገባዎችን ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል።

10. የቦርዱ ስብሰባዎች

1. ቦርዱ ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ሥብሰባ ያካሂዳል።

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም በቦርዱ ሰብሳቢ ጥሪ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛዎቹ ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል።

3. በስብሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።

4. ቦርዱ ማናቸውንም ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ሲሆን ድምፁ እኩል ለእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሠሚብ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

5. ቦርዱ ይህንን አዋጅ ተከትሎ የራሱን የሥብሰባና የአሠራር ሥነ ሥርአት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

9. Evaluate and get approved the structure of the Agency and thereby order the implementation of same;

10. Review and approve short, medium and long as well as annual, capital and recurrent budget plan and report of the Agency and follow up its implementation;

11. Follow and supervise that the Agency properly expend the budget appropriated from the government and its internal revenues;

12. Design ways to strengthen the Agency as well as upgrade its performance;

13. Appoint the Deputy Manager upon his presentation by the General Manager and decide on the recruitment and assignment of other higher management bodies of the Agency;

14. Thrash out and decide on other policy issues pertinent to the Agency;

15. Submit periodic reports to the Council of the Region concerning the performance of the Agency.

10. Meetings of the Board

1. The Board shall meet at least once in three months.

2. Notwithstanding to the provision of sub-Article 1 of this Article, the Board may hold a session at any time whenever the chairperson or one third of the members so request in case of emergency.

3. There shall be a quorum wnere more than half of the members of the Board are present at its meeting.

4. Any decisions of the Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.

5. The Board may draw up its own rules of meeting and working procedure following this proclamation.

11. ስለ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

1. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ ር/መስተዳድር ይሾማል።

2. ዋና ሥራ አስኪያጁ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሠጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ድርጅቱን ያስተዳድራል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ላይ ለድርጅቱ የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት እና በተጨማሪም የሚከተሉትን ያከናውናል፦

ሀ. የድርጅቱን የእለት ከእለት ሥራዎ ች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል፤

ለ. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፤

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት ጋዜጠኞች፣ የቴክኒክ ባለ ሙያዎችንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይቀጥራል ያስተዳድራል፤

መ. የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና የበጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲወሰንለት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ. ለድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ረ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል፤

ሰ. የድርጅቱን የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ወቅታዊ ዘገባዎችን ለቦርዱ እና ለር/መስተዳድሩ ያቀርባል፤

ሸ. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

11. Powers and Duties of the General Manager

1. The General Manager shall be appointed by the Head of the Government upon his recommendation by the Board;

2. The General Manager shall be the Chief Executive Officer of the Agency and shall direct the activity of the Agency with the overall directions of the Board.

3. Without prejudice to the generality of sub-Article 2 of this Article, the General Manager shall discharge specific duties given to the Agency under Article 7 of this proclamation and the following as well:

A. Direct and supervise the day-to-day activities of the Agency;

B. Organize office of the Agency;

C. Employ and administer journalists, technical and supporting staff pursuant to sub-Article 7 of Article 9 of this proclamation;

D. Prepare and submit to the Board short, medium and long as well as annual work program and draft budget of the Agency and thereby implement same upon decision;

E. Effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Agency;

F. Represent the Agency in all its relations with third parties;

G. Submit periodic reports on the activity of the Agency to the Board and the Head of Government.

H. Carryout other functions entrusted to him by the Board.

4. ዋና ሥራ አስኪያጁ ለድርጅቱ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለበታች የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል። ነገር ግን አሱን ተክቶ የሚሰራው ሰው ከ30 ቀናት በላይ ለሚሆን ጊዜ የሚወከል ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

12. ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ

1. የድርጅቱ ም/ሥራ አስኪያጅ በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ ይሰየማል።

2. ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ሆኖ ም/ሥራ አስኪያጁ ከሥራ አስኪያጁ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት በስሩ የተመደቡለትን ዘርፎች ተግባር ይመራል፣ ያስተባብራል፣ እንዲሁም ከሥራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ጊዜ አሱን ተክቶ ድርጅቱን ይመራል።

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. የድርጅቱ የበጀት ምንጭና አስተዳደር

1. የድርጅቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

ሀ. በክልሉ መንግሥት እንደአስፈላጊነቱ ከሚመደብለት በጀት፣

ለ. በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ፣

ሐ. ከሌሎች ምንጮች።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከ (ሀ) እስከ (ሐ) ከተዘረዘሩት ምንጮች የሚገኘው ገቢ በድርጅቱ ስም በሚከፈት የባንክ ሒሳብ ተቀማጭ ሆኖ የድርጅቱን ስራዎች ለማከናወን በየጊዜው ወጭ ይደረጋል።

4. The General Manager may delegate part of his powers and duties to subordinate officials and other employees of the Agency to the extent necessary for efficient performance of the activities of the Agency; provided, however, that, in the case of official who acts on behalf of the General Manager for more than thirty days, the prior approval of the Board shall be required.

12. Deputy Manager

1. The Board upon recommendation by the General Manger of the Agency shall designate the Deputy Manager of the Agency.

2. The Deputy Manager, being accountable to the General Manager, shall direct and coordinate the activities of the sections, which are placed under his responsibility according to the directives of the Manager. He shall also discharge other duties entrusted to him by the General Manager.

3. Direct the Agency in the absence of the General Manager.

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

13. The Agency's Budget Source and its Administration

1. The Budget of the Agency shall be drawn from the following sources;

A. Budget appropriated by the Regional Government as deemed necessary.

B. Service charges collected by the Agency Pursuant to this proclamation; and

C. Other sources.

2. All the revenues drawn from sources specified under sub-Article 1 a to c of this Article shall be deposited in a bank account opened in the name of the Agency and shall be periodically expended for the implementation of the Agency's activities.

3. የድርጅቱ የገቢም ሆነ የንብረት አስተዳዳርና አጠቃቀም በድርጅቱ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ሆኖ መመሪያውን የማሻሻልና የመቀየር ስልጣን የቦርዱ ይሆናል::

14. የሂሳብ መዛግብት

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶችን ይይዛል::

2. የድርጅቱ ሂሳብ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራል::

15. የተሻሩ ህጎች

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል:-

ሀ. የብዙሀን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 56/1993 ዓ/ም፣

ለ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ/ም አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 7::

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

16. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል::

17. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቦርዱ ሊያወጣ ይችላል::

3. The Agency's income as well as property administration and utilization shall be executed in accordance with the Finance and Properly Administration Manual of the Agency and the authority to amend and alter the Manual shall be to the Board.

14. Books of Accounts

1. The Agency shall keep complete and accurate books of accounts and finical records;

2. The account of the Agency shall be frequently audited by the Auditor-General of the Region or by auditors authorized by the Auditor-General.

15. Repealed laws

1. The following are hereby repealed in this proclamation:

A. The Mass Media Agency Establishment proclamation No. 56/2001.

B. Sub Article 5 of Article 6 and sub-article 7 of Article 12 of the provision for the Reorganization of the Amhara National Regional State Executive organs and Determination of their powers and Duties proclamation No. 60/2001.

2. Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall be inapplicable on matter provided herein.

16. Power to Issue Regulation

The council of the Regional Government may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation.

17. Power to Issue Directive

The Board may issue directives necessary to implement this proclamation and regulations there under.

18. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከ ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ/ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት
ባህርዳር

18. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the 8th of July, 2003.

Done at Bahir Dar,
This 8th Day of July 2003

Yosef Retta
President of the Amhara
National Region